UNITED NATIONS
HUMAN RIGHTS COUNCIL

# የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ኮምሽን ባለሞያዎች በ ኢትዮጵያ የተሰጠ መግለጫ

**ነሐሴ 23, 2014**

የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ኮምሽን ባለሞያዎች በ ኢትዮጵያ፣ በኢትዮጵያ መንግስትና በህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ እንደገና ያገረሽው ጦርነት በጣም አስደንግጦታል። ይህ አይነት ግጭት በክ ልሉ ላሉ የሲቪል ማህበረሰብ ከባዱ ኑሮቸውን ሊያባብስ እና ነገሮችን ሊያመሰቃቅል ይችላል ። በተለይ እንዳየነው አሳሳቢ የሆነው በትግራይ ክልል በሲቪል ማህበረሰቡ በመቀለ ህፃናት መጫወቻ ቦታ የደረሰ ጉዳት እና በ አማራ ክልልም መልሶ ያገረሽው ቆቦ ላይ የተደረገ መልሶ ማጥቃት በሲቪል ማህበረሰቡ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው። ስለዚ የጦርነቱን ተሳታፊዎች በአስቸኳይ ትግላቸው በማቆም ወደ ቀድሞ የተስማሙበት የ ድርድር ስምምነት አክብረው እንዲቀጥሉ ጥሪያችንን እናቀርባለን። በተጨማሪም የጦርነቱ ተሳታፊዎች የተባበሩት መንግስታት ይሁን ሌሎች አካላት የሰብአዊ እርዳታ ወደ ትግራይ እንዲዳረስ ፍቃድ መስጠት ይኖርባቸዋል። ከሁሉም በላይ የሰቪል ማህበረሰቡ የሰብአዊ መብቶች እንደ ጤና ፣ የምግብ እና ደህንነትን መጠበቅ ፣ የሁለቱም የግጭቱ ተሳታፊዎች ዋነኛው ቀዳሚ ዓላማ መሆን አለበት።